በታሪክ ውስጥ ያሉ ትምህርቶች አያልቁም፣ ጉዳዩ ከላይ ሲታይ መጥፎ ሊሆን ይችላል፣ ከዚያ ውጤቱ በአላህ ፈቃድ ጥሩ ይሆናል፣ አላየህም እንዴ መጥፎ እና አስቀያሚ ሁኔታዎች ሲከሰቱ? ሆኖም ግን በጉዳዩ ላይ አላህ እንዲህ ይለናል "ለእናንተ ክፉ ነገር ነው ብላችሁ አታስቡት፡ በእውነቱ እሱ ለእናንተ መልካም ነገር ነው። [አን-ኑር፡11]"

እዚህ ላይ ሱራቃ ቢን ማሊክ (ረ.ዐ) ከነብዩ ጋር በተገናኘ በመጀመሪያው ቀን አሳቸውን ለመግደል ቆርጦ ነበር የተነሳው፣ በመጨረሻ የአላህ ፍላጎት ሆነና የእርሳቸው ታማኝ ወታደር ሆነ።

> <u>መልዕክት 4፡</u> ነገሮች ሲታዩ በተቃራኒው የሚሆኑ ቢመስሉም እንኳን በመልካም ተስፋ እንመልከታቸው። እንዲሁም ተስፋ መቁረጥን እና ብስጭትን መተው አለብን። የከውኑ አይነታ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) "በጥሩ ነገር ተስፋ አድርጉ፡ ታገኙታላችሁም" አላሉንም እንዴ በል የተስፋህን መስኮት ከፈት አድርግ አንተ ተስፋ የቆረጥክ፣ የተስፋህ ብርሃን የጨለመውን ክፍል እንዲያሸንፍ ፍቀድለት፣ የጨለማውን ክፍል ማዕዘናት በተስፋ ብርሃን ክሮች አንቆጥቁጥ።

♦♦♦◯♦♦♦

በሰነፍነት የተፈረጀው ቶማስ ኤዲሰን

ቶማስ ኤዲሰን የተወለደው እ.ኤ.አ. በ1847 በአሜሪካ ኦሃዮ፡ ሚላን የሚባል ሥፍራ ውስጥ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ለሦስት ወሮች ብቻ ነበር የተማረው። የትምህርት ቤቱ ዋና አስተዳዳሪ ሰነፍ እና የአዕምሮ ውስንነት ያለበት ልጅ ሆኖ አገኘሁት በማለቱ ከትምህርት ቤቱ እንዲባረር ተደረገ፣ ከዚያም ትምህርቱን እንዲቀጥል አልተፈቀደለትም!!

ለነፍ፡ አካል ጉዳተኛ እና ኋላቀር ነው በሚል ሰበብ በትምህርት ቤቱ የተወገዘው ይህ ሰው፡ አንድ ሺ ዘጠና ሦስት (1093) የፈጠራ ባለቤትነት መብቶችን በስሙ አስመዝግቧል። ይህ መዝገብ አሁንም በአሜሪካን አገር ባለው የፈጠራ ባለቤትነት ቢሮ ተመዝግቦ ይገኛል።

ትምህርት ቤቱ ትምህርቱን አንዳይቀጥል ሲከለክለው፣ እናቱ ይህ በልጁ ላይ የተሰጠው ፍርድ አግባብነት የጎደለው እና የተሳሳተ መሆኑን ስለተገነዘበች በቤት ውስጥ ማስተማሯን ቀጠለች እና አሱም ለዕውቀት ከፍተኛ ፍቀር አንዳለው አንዲሁም በልጅነቱ ግልጽ የሆነ ብስለትን አሳይቷል። ኤዲሰን ከትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር እና አስተማሪዎቹ የበለጠ ብስለት ያለው እና አስተዋይ ልጅ ስለነበረ፡ ብዙ ቁጥር ያላቸው ጥያቄዎችን ይጠይቅ ነበር፡ ይህ የኤዲሰን አብዝቶ መጠየቅ ታዲያ የግንዛቤ እጦት እና የስንፍና ማስረጃዎች እንደሆኑ በማሰብ ነበር አንዲባረር የተደረገው። እውነታው ግን የልጁ አብዝቶ መጠየቅ የአዕምሮውን ንቃት እና የአስተሳሰብ ነጻነትን ነበር የሚያመለክተው።

በኬሚስትሪ መስክ ያደረጋቸውን ሙከራዎች በቤተ-ሙከራ ውስጥ ነበር የሚያከናውነው፤ በሚጠቀምበት ጊዜ እሳት ስለሚነድ እና እሳቱ ሊያቃጥለው ብሎም ሕይወቱን ሊያጠፋው ተቃርቦ የነበረበት ጊዜም አይዘነጋም፡ በመጨረሻም ይህ ክስተት የኤዲሰንን ልጅ መስማት የተሳነው እንዲሆን ዳረገው።

የመጀመሪያው የፈጠራ ሥራውን አንድ ብሎ የጀመረው ድምጽ ቀድቶ እንደገና ለመስማት የሚያገለግን "gramophone" የተባለውን እቃ በማስገኘት ሲሆን በወቅቱ እጅግ ከፍተኛ መጠን በሚባል ዋጋ በአርባ ሺህ (40,000) ዶላር በመሸጥ ያሳለፋቸውን የድህነት፣ የረሃብ እና በቆሸሹ ስፍራዎች መተኛትን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ተሰናበታቸው። በመጨረሻም ለፈጠራ ሥራ ራሱን በመስጠት ኒውዮርክ ውስጥ ትልቅ ቤተ-ሙከራ ማቋቋም ቻለ፣ ይህም በዓለም ውስጥ ላሉት የቤተ-ሙከራ ኩባንያዎች እና ፋብሪካዎች ፈር ቀዳጅ ነበር።

አሌክሳንደር ግራሃምቤል የተባለው ፈላስፋ ንግግርን በኤሌክትሪክ ፍሰት አንደሚሰራጭ የደረሰበት ቢሆንም፡ ይህንን ጠቃሚ ግኝት በንግድ ሚዛን ወደ ሚፈቅድለት እና ለመገናኛነት ወደሚያገለግል መሳሪያነት ወይም ስልክ መለወጥ ግን አልቻለም ነበር፤ ይህንን ተከትሎ "ዌስተርን ዩኒየን" የተባለው ኩባንያ ቶማስ ኤዲሰንን ለአጠቃላይ አገልግሎት የሚውል ስልክ አንዲሠራለት በይፋ የጠየቀ ሲሆን፣ ከጥቂት ወሮች በኋላ ኤዲሰን ይህንን የፈጠራ ሥራ በማስገኘት ለተጠቀሰው ኩባንያ በመቶ ሺህ ዶላር ሽያጭ አካሄደ።

ኩባንያውም የተጠየቀውን ሙሉ ክፍያ ባንዴ ለመክፈል የተስማማ ቢሆንም፡ ኤዲሰን አይሆንም አለ፡ ይልቁንስ የፕሮጀክቱ ስኬታማነት ታይቶ በአሥራ ሠባት ዓመት ክፍያው አንዲከፈለው ጠየቀ። ምክንያቱንም በነዚህ ዓመቶች ውስጥም የአዕምሮ ሰላም አንዲኖረኝ እና የወደፊቱን ግንኙነቴን በዚህ መንገድ ማስጠበቅ ስለምፈልግ ነበር ያለው።

ምንም አንኳን ከአንድ ሺህ በላይ የፈጠራ ሥራዎች በከብር መዝገብ በሥሙ ሰፍረው ቢገኙም፡ ከእርሱ በፊትም ሆነ በኋላ ማንም ያልደረሰበትን ታላቅ ግኝት ያስገኘው ግን የኃይል ማመንጫዎችን ለማቋቋም የሄደበት መንገድ እና የኤሌክትሪክ መብራትን ለቤት እና ለሱቆች ለማሰራጨት የአውታረ መረብ ዝርጋታን ያካሄደበት ነበር። በዚህ ምድር ላይ ከኖሩበት ረዜ አንስቶ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች በሙሉ ሌሊታቸውን በጨለማ ውስጥ ያሳልፉ ነበር፡ ዕድሜ ለሰነፉ ኤዲሰን ይሁን እና ቤቶች፣ ሱቆች፣ እና ከተሞች ወደ ደማቅ እና ብርሃናማነት ተለውጠዋል።

ቶማስ ኤዲሰን የኤሌክትሪክ እና የብርሃን ዘመን መጀመሩን እና የጨለማ ረዜ ማብቂያ አንደደረሰ ሲያስታውቅ ብዙዎች ተሳልቀውበት ነበር። የቶማስ ኤዲሰን ታሪክ ራስን በራስ የማስተማር እና እጅግ አስደናቂ ከሆኑን ታሪኮች መካከል አንዱ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን የሰው ልጅ የፍላጎቱን ሻማ ካቀጣጠለ ጠቢብ ሊሆን አንደሚችል የሚያረጋግጡ ድንቅ ትምህርቶችን እና ታላላቅ አመላካቾችን ይዟል።

ኤዲሰን በአንድ ወቅት "ሁለት በመቶ መነሳሳት እና ዘጠና ስምንት በመቶ ጥረት እና ትጋት ነው ለዚህ ያበቃኝ" ብሎ ነበር የስኬቱን ምስጢር ሲያስረዳ፡ ስለሆነም ታሪክ ሁሌም ከሚያወሳቸው እና ከማይረሳቸው ድንቅ ሰዎች መካከል አንዱ ሆኖ በታሪክ መዝገብ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡ በሳይንስ እና ፈጠራው ዘርፍም የከፍታውን ዳራ ነክቷል ።

…… እሱ በጭራሽ ለተስፋ መቁረጥ እጅ አልሰጠም ……

እሱ በጨለማ ኮሪደሮች ተከቦ እንኳን በተስፋ መቁረጥ ወደኋላ አላፈገፈገም፣ የልጅነት አስተሳሰቡን በመመልከት በሰነፍነት እና በኋላ ቀርነት ቢመለከቱትም በፍፁም ወደፊት ከመጓዝ አላቆመውም ነበር። በመጨረሻም ተስፋ መቁረጥን በመታገሉ የሚገባው የከፍታ ማማ ላይ ደርሷል።

> <u>መልዕክት 5፡</u> ቶማስ ኤዲሰን በሕይወቱ ሰማይ ላይ ያንዣበቡ አስተሳሰቡን ወደ ተስፋ መቁረጥ የሚቀይሩ ኃይለኛ አውሎ ነፋሶች ሳያሸንፉት ተቋቁሞ በመሻገር እንዴት ለስኬት እንደበቃ ከዚህ ታሪክ መማር እንችላለን።

♦♦♦◯♦♦♦

የህልም ዘራፊዎች

ራዕይህን ለማሳካት እንዳትጥር ብሎም እንድትተው ሊያሳምኑህ የሚሞክሩ ሰዎች ይኖራሉ፣ "ጭራሽ የአዕምሮ ህመምተኛ ነህ እንዴ ይህንን እንዴት አሰብከው?" በማለት ያንን ራዕይ ማሳካት እንደማይቻል ይነግሩሃል፣ በሃሳብህ ላይ በማፌዝ እና በመሳለቅ አነርሱ ወዳሉበት ደረጃ እንድትወርድ ለማድረግ ጥረታቸውን ይቀጥላሉ። እንዲህ ህልምህ እንዳይሳካ ያላሰለሰ ጥረት የሚያደርጉትን ሰዎች ሞንቲ ሮበርትስ የተባለው ግለሰብ "የህልም ዘራፊዎች" ብሎ ይጠራቸዋል ስለዚህ ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጆሮህን አትስጥ።

ሞንቲ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረበት ወቅት፡ የክፍሉ ተማሪዎች ስለወደፊት ህልማቸው እንዲጽፉ ከወደ አስተማሪያቸው በኩል ይነገራቸዋል። ሞንቲም ብዙ ቁጥር ያላቸው ለግልቢያ ውድድር የሚያገለግሉ ፈረሶችን፡ ሰፊ የእርሻ መሬት ላይ፡ የማራባት እቅድ እንዳለው እና ባለቤት መሆን እንደሚፈልግ ይጽፋል፤ አስተማሪውም በጣም ዝቅተኛ ውጤት ይሰጠው እና ምክንያቱን ሲያብራራ፡ አንተ ህልሜ ይህ ነው ብለህ የጻፍከው ነገር ከእውነታ የራቀ ስለሆነ ነው ይለዋል፤ አስተማሪውም አክሎ፡ አንድ የጭነት መኪና ጀርባ ላይ የሚኖር ምስኪን ልጅ፡ እንዴት በጣም ሰፊ የእርሻ መሬት ለመግዛት አቅም ሊኖረው ይችላል? ፈረሶችን እና ለመራቢያቸው የሚያስፈልጉትን መሣሪያዎችስ ለመግዛት እንዴት ይቻለዋል? ሽረ ለእርሻው ሠራተኞች የሚከፈል ደመወዝስ ከየት ያመጣል፤ በማለት አስተማሪው ለትንሹ ሞንቲ ከፍተኛ ውጤት ለማግኘት ወረቀቱን እንደገና እንዲጽፍ ዕድል እንደተሰጠው ይነግረዋል፤ ሞንቲም "አንተም ውጤቱን አትቀይር እኔም ህልሜን አልቀይርም" በማለት መለሰለት።

> <u>መልዕክት 6፡</u> ዛሬ ላይ፡ በካሊፎርኒያ ግዛት፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የውድድር ፈረሶችን የሚያሰለጥንበት፣ እጅግ በጣም ሰፊ ቦታ ያለው፣ የተዋጣለት የፈረስ አርቢ ግለሰብ ሆኗል። ምክንያቱም ሞንቲ ህልሙን ማንም እንዲሰርቀው አልፈቀደም!!

♦♦♦◯♦♦♦

ከመልህቁ ራቅ

እንደ ዌልላንድ አባባል ሰዎችን የመልህቅ ዓይነት እና የሞተር ዓይነት ሰዎች ብለን ከሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን። እንግዲያውስ ከመልህቅ ዓይነት ሰዎች በመራቅ የሞተር ዓይነት ሰዎች ጋር ዝምድናችንን ጠበቅ አድርጎ መያዝ ያስፈልጋል። ምክንያቱም የሞተር ዓይነት ሰዎች ግባቸውን ለማሳካት ወደፊት

የሚጓዙ እና ብዙ ደጋፊም ያላቸው ሲሆኑ፤ በአንጻሩ ግን የመልህቅ ዓይነት ሰዎች ቁልቁል ይዘውህ የሚወርዱ ዓይነት ሰዎች ናቸው።

በስኬት ጎዳናህ ላይ "አዎ-ይሆናል" የሚለውን ቃል ለማግኘት "አይ-አይሆንም" የሚለውን ቃል ማስታወስ እና መተግበር እንዳለብህ አስታውስ። ቅን ልቦና ያላቸው ወላጆችህ፣ ጓደኞችህ፣ ዘመዶችህ እንዲሁም የሥራ ባልደረቦችህ እውነተኛ ሥራ እንድታገኝ ቢያስታውሱህም እንኳን ፈጥነህ ተስፋ ለመቁረጥ እጅ አትስጥ። እውነተኛ ሥራህ ሕልምህ ነውና። አሁን ምን ዓይነት ጓደኞች እንዳሉህ ለማወቅ አያጓግትህም።

> <u>መልዕክት 7፡</u> አሁን በዙርያህ ያሉትን ሰዎች በጥንቃቄ ተመልከታቸው እና ራስህን ጠይቅ፣ እነሱ የሞተር ወይንስ የመልህቅ ዓይነት ሰዎች ናቸው?

የበረሃው አንበሳ

ዑመር አል-ሙኽታር በበርቃ ግዛት ውስጥ በምትገኝ አል-በጥናን በምትባል ከተማ ውስጥ ጥሩ አማኝ ተደርገው ከሚወሠዱት ወላጆች በ1858 እ.ኤ.አ ተወለደ። ወላጅ አባቱ ሐጅ ለማድረግ ወደ መካ ሲያቀኑ ነበር ያረፉት።

ጣሊያኖች ወደ ሳይረናይካ እና ትሪፖሊ ከመጡበት ጊዜ አንስቶ ሸንፈትን ተከናንበው ድል እስከተነሱበት ጊዜ ድረስ ሊቢያውያን የትግላቸውን ታሪክ በደማቸው ጽፈው በእምነት እና በታሪካቸው የሚኮሩ ሕዝብ መሆናቸውን እና ማንም ጠመንጃ እና መድፍ የታጠቀ ኃይል ሕይወታቸውን በማጥፋት በእነሱ ላይ ቢጣመር ሊጠፉ እንደማይችሉ ያስመሰከሩበት ጊዜ ነበር። በበርቃ እና በትሪፖሊ ላይ የጣሊያን ጥቃቶች ዜና በመላው አገሪቱ በስፋት ተሰራጭቷል እናም ኦቶማኖችን ለመርዳት እና በባርካ ውስጥ ከነበሩት ጠላት ጋር ለመግጠም

አርበኛው ዑመር አል-ሙኽታር ፊት ለፊት ተሰለፈ። በዚህም የተነሳ "አረንጓዴው ተራራ" በአስተዳዳሪነት መምራት ቢጀምርም የኋላ ኋላ ግን የሙጃሂዶች (ታጋዮች) ጠቅላይ አዛዥ ሆኖ ተመደበ።

ከዕቅዱ መካከል የመከላከል እና በጠላት ውስጥ አድፍጦ መቆየት ሲሆን ጣሊያኖች ቦታዎቻቸውን ለቀው ቢወጡ ሙጃሂዶች አነሱን ያጠቋቸዋል፣ በእነሱ ላይ የከፋ አሟሟትም ያደርሱባቸዋል አንዲሁም በርካታ ምርኮኞችን ይወስዱባቸዋል። ነገር ግን በአስቸኳይ የሚያስፈልጋቸውን በርካታ መሳሪያዎችና ቁሳቁስ አገኘላቸው።

ከዚያ ጣሊያኖች በሙጃሂዶች መካከል የልዩነት ዘሮችን ለመዝራት መሞከራቸውን አንዲሁም አለቃ ዑመር አል-ሙኽታርን ለማባበል ከፍተኛ ገንዘብ በልግስና አቅርበው የተመቻቸ ሕይወት እንደሚኖረው በለሆሳስ ለማስማማት ሞከሩ፣ ሆኖም ግን አልተሳካላቸውም።

እናም ጣሊያኖች በ1927 ከጃጉቡብ ወረራ በኋላ፡ ሙጃሂዶችን ለመለያየት በአረንጓዴው ተራራ እና በሳይሬይካ መካከል እንዲሁም ግብጽ ከምሥራቅ በኩል እና በተቀረው ሴኑሲ መካከል ያሉትን መንገዶች በመቁረጥ በደቡብ በሚገኙ ማዕከላት እነ ዑመር አል-ሙኽታርን እና ሙጃሂዶችን በሰሜን በኩል በማድረግ ሙሉ ለሙሉ ለየብቻ አደረጓቸው። በዚህ ምክንያት ታዲያ ዑመር አል-ሙኽታር የተዳከመ ይመስልሃል? ድንጋጤስ ያደረበት ይመስልሃል? ወደፊት ጉዞውን ከመቀጠል ተስፋ የመቁረጥ ስሜት በልቡ ውል ያለበት ይመስለሃል? በፍጹም!፤ አንዱም ከስተት አላጋጠመውም። ይልቁንስ ከወደ አላህ የመጣ ነገር እንደሆነ በልበ ሙሉነት በማመን ፈገግ ሲል ነበር። በዚሁ ሁኔታም ጦርነቱን ቀጠለ።

ይባስ ብሎ የነበረው የጨለማ ጊዜ እና የተቆላለፈው ነገር ሁሉ ሳይበግረው ደርና በተባለው ስፍራ እና በአከባቢው የሚገኙትን ዋሻዎች በማቆራረጥ ጣልያኖች ከተደበቁበት ወጥተው ከሠራዊቶቹ ጋር እንዲገናኙ እስከሚያስገድዳቸው ድረስ

ግጥሚያውን በማፋፋም ወረራውን ቀጠለ፣ ሁለት ቀን ከፈጀ ከባድ ፍልሚያ በኋላ በጣልያኖች ላይ የድልን ጽዋ ተጎነጨ።

እናም አላህ (ሱ.ወ) ለማዕት ሊያደርገው ሲፈልግ እንደተለመደው አነስተኛ ቡድን፡ በቁጥር ወደ አርባ ገደማ ከሚገመቱ ፈረሰኞች ጋር የጠላትን ቦታ ለመዳሰስ የሙጃሂዶች ወንድሞቹን ማዕከላት ለመፈለግ፡ አስቸጋሪ የሆኑ መንገዶች እና ጫካዎች በሚበዛበት አንድ ሸለቆ ውስጥ አለፈ። የዚህን ጊዜ የጣሊያን ኃይሎች በሰላዮቻቸው አማካኝነት ሁኔታውን ስላወቁ ሸለቆው እንዲከበብ ትዕዛዝ ሰጡ ዑመር አል-ሙኽታርስ ምን ተሰማው? የተመረጡት እና አብረውት በጠላት መካከል የነበሩትስ? ኋላ ላይ ውጊያ ተካሂዶ የነበረ ቢሆንም፣ ብዙ ሰዎች እና የጠላት የመጠባበቂያ ከምችት ቢኖርም፡ ሙጃሂዶች ያን ሁሉ መከራ ጥሰው ወደ ምዕራባዊው የሱልጣኔት ክፍል ደረሱ።

ከዚያ ሌላኛው የጣሊያኖች ኃይል ተገረመ፣ እናም ጥይታቸው ሊያልቅ ስለነበረ አዲስ ጦርነት ውስጥ ገቡ፡ ከሙኽታር ጋር የቀሩትን ሁሉ ገደሏቸው፣ እንዲሁም ፈረሱን ገደሉበት፣ ብቻውንም ቀረ፣ እናም እጁ እስኪቆስል ድረስ ብቻውን መታገሉን ቀጠለ፣ ጠላቶቹም በዙ፡ አካበቡት፡ በመጨረሻ ተሸነፈ፡ በትዕዛዛቸው መሠረትም ያዙት ግን ማንነቱን አያውቁም ነበር። ከዚያ ዑመር እንደሆነ ሲታወቅ በመርከብ አሳፍረው ወደ ሱሳ የላኩት ሲሆን ከዛም ወደ ታሰረበት ቤንጋዚ ተወሰደ።

ሙጃሂዱ ዑመር አል-ሙኽታር በብረት ታስሮ እና በየአቅጣጫው በጠባቂዎች ተከቦ ወደ ችሎት ቀረበ፤ የፍርድ ሂደቱ በቅርጽም ሆነ በይዘት የይስሙላ የሚባል ዓይነት ነበር፤ የፍርድ ሂደቱ ከመጀመሩ ከአንድ ቀን በፊት ነበር የስቅላት ቦታውን እና ቅጣቱን ለማስፈጸም ዝግጅቱን ያጠናቀቁት። የፍርድ ሂደቱ ከጅምር እስከ ማብቂያ ድረስ አንድ ሰዓት ከአሥራ አምስት ደቂቃ (1፡15) የፈጀ ሲሆን የሞት ፍርዱም በአል-ሙኽታር ላይ ተላለፈ። ጀግናውም "በእርግጥ እኛ ለአላህ ነን ወደ እርሱም ተመላሾች ነን። [አል-በቀራህ፡ 156]" በማለት ፍርዱን ተቀበለ።

ረቡዕ መስከረም 11 ቀን 1931 ዓ.ም ጣሊያኖች በሙጃሂዱ ዑመር አል-ሙኽታር ላይ የሞት ፍርዱን በስቅላት ፈጸሙ። ሙኽታር በመጀመሪያው ስቅላት አለመሞቱን ባወቁ ጊዜ ልባቸው በፍርሃት ተውጦ በሽብር ተሞልቶ ለሁለተኛ ጊዜ ስቅላቱን ደገሙት፤ አሱም አረፈ። ከዛ በኋላ ቤንጋዚ ውስጥ ወዳለው የአል-ሰብር መቃብር ወሰዱት፤ ንጹህ ሰውነቱን በተጠናከረ ኮንክሪት በገነቡት እጅግ ጥልቅ በሆነ መቃብር ውስጥ ቀበሩት፣ ዜጎችም ሰውነቱን እንዳያወጡት በመፍራት በመቃብሩ ላይ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲጠብቀው አንድ ወታደር ተመድቦ ይጠብቅ ነበር።

> <u>መልዕክት 8፡</u> ሙጃሂዱ ሙኽታር ልቡን በተስፋ መቁረጥ ቢከፍት እና በመጀመርያው መሰናክል ተሸንፎ ቢሆን ኖሮ፣ የትግል ዘር ፍሬውን ባላፈራ እና ሊቢያ የጣሊያን ቅኝ አገዛዝን ከምድሪቷ በማባረር ነጻነቷን ባላገኘች ነበር።

ያለፈው ላይመለስ አልፏል

ያለፈውን ጊዜ ማስታወስ፣ ከእሱ ጋር ለመግባባት መሞከር እና ማሰላሰል፣ በአሰቃቂ ሁኔታ ለደረሰብህ ነገር ከልክ በላይ ማዘን፡ ሞኝነት እና አብደት ሲሆን፣ የአሁኑን ሕይወት ማባከን እና የወደፊት ፍላጎትህንም መግደል ነው።

ብልሆች ዘንድ፣ ያለፈው ፋይላቸው ተጣጥፎ ይቀመጣል እንጂ በጭራሽ አይወሰም፣ በመርሳት ማረሚያ ቤት ውስጥ በጠንካራ ገመድ ታስሮ ይቀመጣል፣ እንዲወጣም በጭራሽ አይፈቀድለትም፣ በሩም ተዘግቶበታል እና ብርሃንን አያይም። ምክንያቱም ያለፈ ነገር፡ የሞተ እና ያለቀለት ሲሆን፡ ሐዘን አይመልሰውም፣ ጭንቀትም አያስተካክለውም፣ ምንም ነገር አያድሰውም።